# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

## የፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት ያወጣውን መግለጫ አስመልክቶ ከኢሕአፓ የተሰጠ ይፋዊ መግለጫ!

እንደሚታወቀው በተደጋጋሚ፣ “መንግሥት ሕግ የማስከበር ሚናውን መወጣት አለበት!” እያልን ድምፃችንን ስናሰማ ቆይተናል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጠሩትም ሁከቶችና ብጥብጦችም ራሱን “የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት/ግንባር” የሚለው ኃይል ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ ስለመሆኑ ፀሐይ የሞቀው፣ አገር ያወቀው ሲሆን፣ በመላ ኢትዮጵያ ለተከሰቱት የሠላምና ፀጥታ እጦቶች ከፍተኛውን ሚና ወጫወቱ ዕሙን ነው። መንግሥትም በዚህ አደገኛና ከፋፋይ ቡድን ላይ የሚወስደውን እርምጃ እንደምንደግፍና አባሎቻችንም ጭምር ከመንግሥት የፀጥታና የሕግ አስከባሪዎች ጎን እንዲቆሙ በጥቅምት 26/2013 ዓ.ም ባወጣነው መግለጫ ላይ በግልጽ አንጸባርቀናል።

አሁንም ሆነ ወደፊት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍንና የዜጎች ተዘዋውሮ የመኖር፣ ሃብትና ንብረት የማፍራት፣ እንዲሁም በፈለጉት አጀንዳና ዓላማ ሥር በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ የመደራጀት፣ ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብት እንዳላቸው በመግለጫዎቻችንና በጽሑፎቻችንም ውስጥ በአጽንኦት መግለጻችን ይታወቃል። በአሁኑም የመንግሥት “የሕግ ማስከበር” እንቅስቃሴ ወቅት ይህ የዜጎች መብት እንዳይጣስ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ እንጠይቃለን። ለዚህም ክቡር ዓላማ ዋጋ እየከፈሉ ላሉት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላትና የጸጥታ ኃይሎች በሞላ ከፍተኛ አክብሮት እንዳለን ለመግለጽ እንፈልጋለን። አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችንም ይህንን ክቡር የሆነ ዓላማ እና ግብ ለመደገፍ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥሪያችንን በድጋሚ እናስተላልፋለን።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ የኢትዮጵያ የተፎካካሪ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት (የጋራ ም/ቤት) አመራሮች ኢሕአፓ እንደ ምክር ቤት አባልነቱ ለውይይት ሳይጋበዝ፤ ግልጽ አቋም በያዝንበትና ደጋግመን እንዲከበር የጮኽንለትን የሕግ የበላይነት የማስከበር ግብግብ “በድርድርና በውይይት እንዲጠናቀቅ” መፈለጋቸውን አይተናል። ይህን የጋራ ም/ቤት አመራሮች አቋም ኢሕአፓ እንደ አባልነቱ ያልተወያየበትና ያልመከረበት መግለጫና ማብራሪያ በመሆኑ ፓርቲያችን በጥብቅ ይቃወመዋል። የጋራ ም/ቤቱ አመራሮች በም/ቤቱ ስም ከሕወሓት ጋር ድርድር ይካሄድ ማለታቸውንም ኢሕአፓ እንደማይቀበለው አጥብቀን እንገልጻለን። ከዚህ በኋላም የጋራ ም/ቤቱ ፓርቲዎች በተናጠል አቋም የያዙበትን አጀንዳና ፖለቲካዊ አቋም ሳያወያይና ምክክር ሳይደረግበት በምንም ዓይነት በመገናኛ ብዙኃን ላይም ሆነ፣ በየትኛውም የማኅበራዊ ድረ-ገጽ ላይ እንዳያወጣ በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።

በተጨማሪም የጋራ ም/ቤቱ አመራሮች በም/ቤቱ ስም ባወጡት መግለጫ ላይ እንዳንጸባረቁት፣ በምድር ላይ ያለውን ሁኔታ በአግባቡ ባላገናዘበ መልኩ ሲሆን፣ በመከላከያ ሠራዊቱ ላይ ጥቃት ያደረሰውን እና የሀገርና

Phone :0911405427/0946240724/0911393535 Email:eprp@eprp-ihapa.com

የሕዝብ ንብረት የሆነውን፣ "በትግራይ ክልል ውስጥ የነበረውን የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ንብረት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሬ ሥር አውያልሁ!" በማለት በህገ-ወጥ ተግባር እንደተሰማራ በይፋ ከሚናገረው ህወሓት ጋር ድርድር ይካሄድ ማለታቸውንም ኢሕአፓ እንደማይቀበለው አጥብቀን እንገልጻለን። ኢሕአፓ ስለብሄራዊ እርቅ፣ ስለደርድርና ሀገራዊ መግባባት የነበረውና አሁንም ያለው ቁርጠኛ አቋም የማይናወጥ ነው። ሆኖም እነዚህ ሁሉ አግባብ ባለው ቦታና ሁኔታ ውስጥ ሊታዩ ይገባል የሚል ጽኑ አቋም አለው። የሀገርን መከላከያ ሠራዊት ከረሸኑና የሀገር መከላከያ የሆኑ ንብረቶችንም በጉልበት ከነጠቁ በኋላ፣ "ጉዳዩ የብሄራዊ እርቅ ጉዳይ ነው፣" ማለት አግባብነት ያለው አይደለም። ሕወሓት በመከላከያ ይዞታ ላይ ጥቃት ከሰነዘረበት ቅጽበት አንስቶ፣ ጉዳዩ "የሕግ የበላይነት ከማስፈንና ሕግን ከማስከበር አንፃር የሚታይ እንጂ፣ በምንም ሂሳብ ፖለቲካዊ ይዘት የለውም።

ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ እፎይ እንዲልና የሰላም አየር እንዲተነፍስ ጽኑ ፍላጎት አለው። ኢሕአፓ በትግራይ ውስጥ ሆኖ የታገለ ፓርቲ በመሆኑ የትግራይን ሕዝብ ሥነልቦና በሚገባ ያውቃል፤ ከፍ ያለ ፍቅርና አክብሮትም አለው። ይህ ሕዝብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከአፈናና ከግዞት እንዲላቀቅ ይፈልጋል፤ በሀገራችን ውስጥም ፈንጥቃ የነበረች የዲሞክራሲ ጭላንጭል እንዳትዳፈን የበኩሉን ትግል የሚያካሂድ ፓርቲም ነው - ኢሕአፓ።

በመሆኑም፣ ይህ ሕግን የማስከበር ተጋድሎና ትንቅንቅ ተጠናክሮ በሀገር መከላከያ ሠራዊትም ሆነ በኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይሎች እንዲቀጥል ኢሕአፓ ሙሉ ድጋፉን ያስተላልፋል። አሁንም ወደፊትም የኢትዮጵያ እና የዜጎቿ ሠላም፣ ዲሞክራሲና ልማት እውን እንዲሆን የድርሻውን ይወጣል።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥቃት መካችነት ከአስከፊ ጦርነት ትወጣለች!**
**ኢትዮጵያ አንድነቷ ተከብሮ ለዘላለም ትኑር!**
**ኢሕአፓ ለተሻለ ነገ!**

**ጥቅምት 30/2013 ዓ.ም…. አዲስ አበባ!**